## የኢትዮጵያ ፡ በጀት ።

### ከቡልቻ ፡ ደመቅሳ*

### የኢትዮጵያ ፡ በጀት ፡ ታሪካዊ ፡ መግለጫ ።

የመንግሥት ፡ በጀት ፡ ማደራጀትና ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ ማውጣት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የገንዘብ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ ነው ። በዓመታዊ ፡ በጀት፡ መገልገል ፡ መጀመሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ከተደረገው ፡ ጠቅላላ ፡ መሻሻል ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ነው ።

የአሁኑ ፡ በጀት ፡ በውስጡ ፡ የተመለከተውን ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ለማድረግ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጥና ፡ የመንግሥቱን ፡ የወጭና ፡ የገቢ ፡ ግምት ፡ ለማገናኘት ፡ የሚረዳ ፡ መምሪያ ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ የበጀት ፡ ዓላማዎች ፡ የመጀመሪያው ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ከ፲፱፻፵፯ ፡ በፊት ፡ በጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ ወጪ ፡ ይፈቀድበት ፡ በነበረው ፡ በማዘዣ ፡ አማካይነት ፡ ይከናወን ፡ ነበር ።[1] ነገር ፡ ግን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መግለጫ ፡ የሚሰጥ ፡ የወጪና ፡ የገቢ ፡ ግምት ፡ አልነበረም ። የበጀት ፡ መግለጫዎች ፡ በየጊዜው ፡ ይታተሙ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ መግለጫዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ የወጡትን ፡ ማዘዣዎች ፡ በአሕጽሮተ ፡ ጽሑፍ በማቅረብ ፡ በጀቱን ፡ በመንግሥት ፡ የሥራ ፡ ፕሮግራምና ፡ የወጪ ፡ ዓይነት ፡ መሠረት ፡ በአርእስት ፡ ከማዘጋጀት ፡ አላለፉም ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የታተመው ፡ የመጀመሪያው ፡ የመንግሥት፡ በጀት የወጣው ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡[2] ሲሆን ፡ የ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ን ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ ሸፍኖ ፡ ነበር ።[3] ለ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አንድ ፡ በጀት ፡ ታውጆ ፡ ነበር ፤[4] ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በጀት ፡ የወጣው ፡ የተባለው ፡ ዓመት ፡ ሊያልቅ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ሲቀረው ፡ ነበር ።

---

* በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር ፤

1. ይህ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በያንዳንዱ ፡ በጀት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ የድንገተኛ ፡ ወጪዎች ፡ መጠባበቂያ ፡ ለሚወጣው ፡ ገንዘብ ፡ የወጪ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሆኑን ፡ ይቀጥላል ። ገጽ ፡ 366 ተመልከት።
2. አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፹፩/፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፬ ። በመሠረቱ ፡ የ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጨማሪ ፡ በጀት ፡ የነበረው ፡ ዓመቱ ፡ ተፈጽሞ ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ በአዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፹፰/፲፱፻፴፰፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፩ ፡ ወጣ ።
3. የኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ ከአውሮፓ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ይለያል። አንደኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዓመት ፡ የሚጀመረው እንደ ፡ አውሮፓ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ሰፕቴምበር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ (በዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰፕቴምበር ፡ ፲፪ ፡ ቀን) ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዓመተ ፡ ምሀረት ፡ ከአውሮፓ ፡ ዓመተ ፡ ምሀረት ፡ በ፰ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ያንሳል ። ስለዚህ ፡ የ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር) ፡ ሰፕቴምበር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም፡ (እንደ ፡ አውሮፓ ፡ አቆጣጠር) ፡ ነበር ።

   የበጀት ፡ ዓመት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፻፳፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ፡፲፰ኛ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ ዓመት ፡ ነበር ። በበጀት ፡ ዓመት ፡ አዋጁ ፡ መሠረት ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ ሐምሌ ፩ ፡ ቀን ፡ እንዲጀመር ፡ ተደረገ ።

ምንም ፡ ዓይነት ፡ በጀት ፡ ሳይወጣ ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አንድ ፡ የበጀት ፡ መግለጫ ፡ አተመ ፤ የታተመውም ፡ በማስታወቂያ ፡ ነበር ።[5] ይህም ፡ ዓመቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ስለ ወጣና ፡ ፓርላማው ፡ መክሮበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያጸደቀው ፡ ሕግ ፡ ሣይሆን፡ የሚኒስቴር ፡ ማስታወቂያን ፡ መልክ ፡ ስለያዘ ፡ እንደ ፡ ደንበኛ ፡ በጀት ፡ ሊቆጠር የሚችል ፡ አልነበረም ። ስለዚህ ፤ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የአለፈውን ፡ ዓመት ፡ የመንግሥት ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ የሚያሳይ ፡ መግለጫ ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ የገንዘብ ፡ አቋም ፡ ጠቃሚ ፡ መግለጫ ፡ ሰጥቷል ።

ተከታዩ ፡ የመንግሥት ፡ በጀት ፡ የታተመው ፡ በ፲፱፻፵፬ ፡[6] ሲሆን ፤ ያ ፡ ዓመት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የበጀት ፡ መሻሻል ፡ የመጀመሪያ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ የ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጀት ፡ ዓመቱ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ስላልወጣ ፡ በትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ በጀት ፡ ማለት ፡ ለገንዘብ ፡ ቊጥጥር ፡ የሚረዳ ፡ የወደፊት ፡ የገቢና ፡ የወጪ ፡ ግምት ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ። ነገር ግን ፡ ይህ ፡ በጀት ፡ የወጣው ፡ አዲሱ ፡ የተሻሻለው ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ፓርላማው ፡ መክሮበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ፡ ካጸደቀው ፡ በኋላ ፡ ነበር ። በተጨማሪም ፡ ይህ ፡ በጀት ፡ ዓመታዊ ፡ የመንግሥት፡ በጀት ፡ ያለማቋረጥ ፡ መታወጅ ፡ የጀመረበት ፡ ዘመን ፡ ሆነ ፤ የ፲፱፻፵፱ና ፡ የ፲፱፻፶ ፡ የበጀት ፡ አዋጆች ፡ ከበጀት ፡ ዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ብዙ ፡ ዘግይተው ፡ ቢወጡም ፡ የዘመኑን ፡ በጀት ፡ ቢያንስ ፡ በከፊል ፡ ለመቆጣጠር ፡ ረድተዋል ።

## ሕጋዊ ፡ አቋም ፡

ስለ ፡ መንግሥት ፡ በጀት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ፡ የተነገረው ፡ በ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፭ ፡ እንደሚከተለው ነው ።

> "በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ የሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ አመልካችነት ፤ በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ መምሪያና ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እየተመከረበት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እየተፈቀደ፡ በሚኒስቴሩ ፡ ክፍል ፡ የሚወጣው ፡ ያመቱ ፡ ሒሳብ ፡ (ቢድዠ) እየታሰበ ፡ እንዲወጣ ፡ በሕግ ፡ ተወስኗል ።"

ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ እንደ ፡ ሚኒስቴር ፡ መ/ቤት ፡ ማስታወቂያ ፡ ለወጣው ፡ የ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጀት ፡ መሠረት ፡ ባይሆንም ፤ ለ፲፱፻፵፬ና ፡ ለ፲፱፻፵፭ ፡ በጀቶች ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ መሠረት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

የ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተተክቷል ። በቀጥታ ፡ በጀትን ፡ የሚመለከቱት ፡ የአዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ፡ እስከ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፰ ፡ ከዚህ ፡

4. አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፹/፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አምስተኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፲፱ ።
5. የማስታወቂያ ፡ ቍጥር ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፬ ።
6. የበጀት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፻፳ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፩ ።

በታች ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፈዋል ።[7] እነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ ካስከተሏቸው ፡ ለውጦች ፡ አንዱ ፡ በጀቱ ፡ በፓርላማው ፡ ተፈቅዶ ፡ ከአዲሱ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ አስቀድሞ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የፓርላማው ፡ ተግባር ፡ በበለጠ ፡ ተገልጿል ። ፓርላማው ፡ በበጀቱ ፡ ላይ ፡ አንቀጽ ፡ በአንቀጽ ፡ ድምጽ ፡ መስጠት ፡ ሲኖርበት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ካቀረበው ፡ ጠቅላላ ፡ ወጪ ፡ በላይ ፡ እንዳይፈቅድ ፡ ታግዷል ።

ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሌላ ፡ በጀትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ቀዋሚ ሕጎች ፡ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡[8] የወጣው ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር የሚወስን ፡ ትእዛዝና ፡ በ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወጥቶ ፡ በኋላ ፡ የተሻሻለው ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ አዋጅ ፡[9] ናቸው ። የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ በሚወስነው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ሚኒስትሮች ፡ የወጪ ፡ ግምታቸውን ፡ እስከ ፡ ሐምሌ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ማቅረብ ፡ ሲኖርባቸው ፤ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩም ፡ በጀቱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለሚንስትሮች ፡ምክር፡ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት። በበጀት ፡አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ የሚጀመረው ፡ ሐምሌ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ በጀቱ ፡ ከመጋቢት ፡ ፲፬ ፡ በፊት ፡ ለፓርላማው ፡ መቅረብ ፡ አለበት ፡ ለመረዳት ፡ እንደሚቻለው ፡ በበጀቱ፡ ዓመት፡ አዋጅ፡ ውስጥ፡ የተመለከተው፡ ሰንጠረዥ ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ በሚወስነው ፡ ትእዛዝ ፡የተወሰነውን ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ግምት ፡ የማቅረቢያ ፡ ቀን ፡ እንዳይሠራበት ፡ አድርጎታል ።

---

7\. "አንቀጽ ፡ ፻፲፬ ። ማናቸውም ፡ የመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ በሕግ ፡ እንደተፈቀደው ፡ ካልሆነ በቀር ፡ ወጪ ፡ አይሆንም ።

አንቀጽ ፡ ፻፲፭ ። የበጀት ፡ ዓመት ፡ በልዩ ፡ ሕግ ፡ ይወሰናል ። በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፈቃድና ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለመጪው ፡ ዓመት ፡ በሥራ፡ ላይ ፡ የሚውለው ፡ በጀት ፡ የሚፈቀድበትን ፡ በጀት ፡ አሳብ ፡ ጨምሮ ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ እያስናዳ ፡ በየዓመቱ ፡ ለፓርላሜንቱ ፡ ያቀርባል ።

አንቀጽ ፡ ፻፲፮ ። ፓርላሜንቱ ፡ ያቀረበለትን ፡ በጀት ፡ በዝርዝር ፡ መርምሮ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ድምጽ ፡ ይሰጥበታል ። ስለወጪ ፡ በበጀቱ ፡ ከተመለከተው ፡ ከጠቅላላው ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ መጨመር ፡ አይችልም ። በተባለው ፡ በጀት ፡ ውስጥ ፡ የቀረበውን ፡ ለድንገተኛ ፡ ወጪ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ይወስናል ። ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ በበጀቱ ፡ ላይ ፡ ድምጽ ፡ መስጠቱን ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ አዲሱ ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ ከሚጀመርበት ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ መጨረስ ፡ አለበት ።

አንቀጽ ፡ ፻፲፯ ። በአንቀጽ ፡ ፻፲፮ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ የቀረበውን ፡ የሕጉን ፡ አሳብ ፡ ፓርላሜንቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነና ፡ አዲሱ ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ያልታወጀ ፡ እንደሆን ፡ አዲሱ ፡ የበጀት ፡ ሕግ ፡ እስኪታወጅ ፡ ድረስ ፡ የዚያው ፡ የቀድሞው ፡ ዓመት ፡ በጀት ፡ ሲሠራበት ፡ ይቆያል ።

አንቀጽ ፡ ፻፲፰ ። ማናቸውም ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ በሚያስቸኩል ፡ አኳኋን ፡ ያስፈለገ ፡ እንደሆን ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ሚኒስትር ፡ ወይም ፡ ሚኒስትሮች ፡ ተጨማሪውን ፡ በጀት ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያቀርባሉ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ሲፈቅድ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ አዘጋጅቶ ፡ አስቀድሞ ፡ ለሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ቤት ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።"

8\. አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ እና ፡ ፳፪ ፡ (ሀ) ፡ ትእዛዝ ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሁለተኛ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፩ ።
አዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፷፱ ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አስራ ፡ ስምንተኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፲፫ ፡

9\. በአዋጅ፡ቊጥር ፡ ፪፻፶፰ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሃያ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፰ ፡ እንደተሻሻለ ።

እርግጥ ፡ በጀቶቹ ፡ ራሳቸው ፡ የበጀት ፡ ዓመቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ የሕግ ፡ ኃይል ፡ የሌላቸው ፡ በየዓመቱ ፡ የሚወጡ ፡ ሕጐች ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ዓመታዊው ፡ በጀት ፡ የተፈቀዱትን ፡ ወጪዎችና ፡ የገቢዎች ፡ ግምት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ተጨማሪ ፡ በጀት ፡ ለፓርላማ ፡ ሳይቀርብ ፡ በበጀቱ ፡ ወጪዎች ፡ ውስጥ ፡ ሊደረጉ ፡ በሚችሉት ፡ ለውጦች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ወሰን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎችንም ፡ ይይዛል ። እነዚህም ፡ ድንጋጌዎች ፡ የበጀት ፡ ዓመቱ ፡ ሲፈጸም ፡ የሕግ ኃይላቸውን ፡ የሚያጡ ፡ ናቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በተመሳሳይ ፡ መስመሮች ፡ እየተደጋገሙ ፡ ወጥተዋል ። እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጀት ፡ ውስጥ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተጽፈዋል ።

"፰ ፡ በበጀት ፡ የተፈቀደውን ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ከአንድ ፡ አርእስት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አርእስት ፡ ወይም ፡ ከንዑስ ፡ አርእስት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ዝርዝር ፡ ወደሌላ ፡ በሚከተሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ለማዛወር ፡ ይቻላል ።

(ሀ) በአንድ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ ከአንድ ፡ የንዑስ ፡ አርእስት ፡ ዝርዝር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ለማዛወር ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጸማል ። የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ እርሱ ፡ በወሰነው ፡ መሠረት ፡ የተባለውን ፡ የማዘዋወር ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ሌሎችን ፡ ሹማምንት ፡ ሊወክል ፡ ይችላል ።

(ለ) በአንድ ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ ከአንድ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ወደሌላው ፡ ንዑስ ፡ አርእስትና ፡ ከአንድ ፡ የመደበኛ ፡ ወጪ ፡ አርእስት ፡ ወደ ፡ ካፒታል ፡ ወጪ ፡ ለማዛወር ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር፡ ቤትን ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል ።

(ሐ) ድንገተኛ ፡ ወጪ ፡ ከሚለው ፡ አርስርት ፡ ወደሌላው ፡ ለማዛወር፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤትን ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል ።

(መ) ድንገተኛ ፡ ወጪ ፡ ከሚለው ፡ አርእስት ፡ በስተቀር ፡ ከሌላ ፡ አርእስት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ በማዛወር ፡ ለደመወዝና ፡ አበል ፡ ከተፈቀደው ፡ በላይ ፡ ወጪ ፡ ለማድረግ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይፈቀድም ።

(፱) ባለፈው ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ በበጀት ፡ ገንዘብ ፡ ተፈቅዶላቸው ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ ሲዘጋ ፡ ሥራዎቹና ፡ አገልግሎቶቹ ፡ የሚቀጥሉ ፡ ሲሆን ፤ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ አገልግሎቱ ፡ በሕግ ፡ ግዴታ ፡ የተገባበት ፡ መሆኑንና ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚመለከተው ፡ ከዘመኑ ፡ የበጀት ፡ አርእስት ፡ ላይ ፡ ለመክፈል ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ከአረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ሂሣቡን ፡ ከድንገተኛ ፡ ወጭ ፡ ሊከፍል ፡ ይችላል ።

(፲) የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሲፈቅድና ፡ እንዲሁም ፡ ተጨማሪ ፡ መደበኛ ፡ ገቢ ፡ የሚገኝ ፡ መሆኑን ፡ ሲያረጋግጥ ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጀት ፡ አዋጅ ፡ ከተፈቀደው ፡ በአንቀጽ ፡ ፰ ፡ ከተገለጸው ፡ በላይ ፡ ለአንዳንድ ፡ የመንግሥት ፡ አስቸኳይ ፡ ሥራዎች የሚያስፈልጉትን ፡ ወጪዎች ፡ በዚህ ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጀት አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፰ ፡ ከተመለከተው ፡ መደበኛ ፡ ወጪ ፡ አስር ፡ በመቶ ፡ የማይበልጥ ፡ ሆኖ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ እንዲከፍል ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ ተፈቅዶለት ፡ ታዟል ።"

የነዚህም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ዓላማ ፡ የመንግሥቱ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የተጨማሪ ፡ በጀት ፡ አዋጅ ፡ እንዲወጣ ፡ ሳይጠይቁ ፡ በመጀመሪያው ፡ በጀት ፡ ወሰን ፡ ውስጥ ፡ አለችግር ፡ እንዲሠሩ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ በአጥጋቢ ፡ ሁኔታ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋሉም ። ከ፲፱፻፶፫ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ዓመት ፡ ተጨማሪ ፡ በጀት ፡ መጠየቁ ፡ አልቀረም ። በ፲፱፻፶፰ ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ውስጥ ፡ ተጨማሪ ፡ በጀት ፡ ያልተጠየቀው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ፺ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በበጀቱ ፡ ውስጥ ፡ በመጻፉ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

## የበጀት ፡ ሥሌዳ ፡

በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ በኩል ፡ የበጀት ፡ ሥሌዳውን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሦስት ፡ ነጥቦች ፡ በሕግ ፡ ተወስነዋል ። የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ በሚወስነው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ሚኒስትሮች ፡ የበጀት ፡ ግምታቸውን ፡ እስከ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ፤ ይህ ፡ በጀት ፡ በበጀት ፡ ዘመን ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ለፓርላማ ፡ መቅረብ ፡ ሲኖርበት ፡ ፓርላማውም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፤ ከአዲሱ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ እስከቀድሞ ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ ከሰኔ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ በጀቱን ፡ አንቀጽ ፡ በአንቀጽ ፡ እንዲነጋገርበትና ፡ ድምጽ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ያስፈልጋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዳየነው ፡ ሁሉ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ አዋጅ ፡ መውጣት ፡ ከነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጊዜው ፡ ያለፈ ፡ ድንጋጌ ፡ አድርጎታል ።[10] ስለዚህ ፡ ሥሌዳውን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነጥቦችን ፡ የሚወስኑ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ አዋጅ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣው፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ናቸው ። የሥሌዳው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ደረጃዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፩ ፤ ሰኔ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ በጀቱ ፡ ሊዘጋጅለት ፡ ከታቀደው ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ዓመት ፡ አስቀድሞ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የተከታዩ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ የወጪ ፡ ግምት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለየሚኒስትሮቹ ፡ ደብዳቤ ፡ ያስተላልፋል ።

፪ ፤ ደብዳቤው ፡ ሚኒስትሮቹ ፡ የበጀት ፡ ግምታቸውን ፡ ከመስከረም ፡ ፴ በፊት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ያሳስባል ። ስለዚህ ፡ ሚኒስትሮቹ ፡ የበጀት ፡ ግምታቸውን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ከ፫ ፡ ወር ፡ በላይ ፡ አላቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

፫ ፤ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የበጀት ፡ ግምቱን ፡ ከታኅሣሥ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ። ስለዚህ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከየሚኒስቴሮች ፡ የቀረበለትን ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ አቀነባብሮና ፡ አጥንቶ ፡ ለማቅረብ ፡ ፫ ፡ ወሮች ፡ አሉት ።

10. የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከሚወስናቸው ፡ ቀናት ፡ በስተቀር ፡ የሚኒስቴሮች ፡ የበጀት ፡ ግምቶች ፡ የሚቀርቡበት ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ አልተወሰነም ። ይህ ፡ አንዳንድ ፡ ችግሮችን ፡ ከመፍጠሩም ፡ በላይ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብዙ ፡ ሚኒስትሮች ፡ የበጀት ፡ ግምታቸውን፡በጊዜ ፡ ያላቀረቡበትን ፡ ምክንያት፡ ይገልጻል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ የሚወስነው ፡ ትእዛዝ ፡ ሚኒስትሮች ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ ለማቅረብ ፡ አላፊነት ፡ እንዳለባቸው ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ከላይ ፡ የተሰጠው ፡ ማብራሪያ ፡ ለበጀት ፡ ግምት ፡ ፈጽሞ ፡ አለመቅረብ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ።

፬ ፤ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በበጀቱ ፡ ላይ ፡ ለሁለት ፡ ወር ፡ ተኩል ፡ ከተነጋገረና ፡ አስፈላጊዎቹን ፡ ማሻሻያዎች ፡ ካስገባ ፡ በኋላ ፡ መጋቢት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ለፓርላማ ፡ ረቂቅ ፡ የበጀት ፡ አዋጅ ፡ ያቀርባል ።

፭ ፡ ፓርላማው ፡ በረቂቅ ፡ አዋጁ ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ ክርክር ፡ ከሰኔ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡ የተቀበለውንም ፡ በጀት ፡ ሰኔ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማቅረብ ፡ ይገባዋል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ሲያጸድቁት ፡ የበጀት ፡ አዋጅ ፡ ሆኖ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ ይወጣል ።

፮ ፤ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የገንዘብ ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ የተፈቀደውን ፡ በጀት ፡ ዝርዝር ፡ ከሰኔ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ለሚኒስቴሩ ፡ የበጀት ፡ ክፍያ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ያስተላልፋል ።

እንግዲህ ፡ ፲፩ ፡ ወራት ፡ ተኩል ፡ የፈጀው ፡ የበጀት ፡ ሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አዲሱ ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ ሊጀመር ፡ ፪ ፡ ሳምንት ፡ ሲቀረው ፡ ይፈጸማል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ መነሳት ፡ ያለበት ፡ የገቢና ፡ የወጪ ፡ ዝርዝር ፡ከበጀቱና ፡ ከተጨማሪው ፡ በጀት ፡ ጋር ፡ እየተነፃፀረ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ለፓርላማው ፡ መቅረቡ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚደረገው ፡ በበጀቱ ፡ ዙር ፡ የመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ የበጀት ፡ ዘመኑ ፡ ከተፈጸመ ፡ ከአራት ፡ ወራት ፡ ባልበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

## የበጀት ፡ ዝግጅት ።

### የወጪ ፡ ግምት ።

በጣም ፡ የሚያስቸግረውና ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጀው ፡ በየክፍሉና ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ የበጀት ፡ ወጪ ፡ መሰብሰቡ ፡ ነው ። ይህ ፡ የበጀት ፡ ወጪ ፡ የሚሰበሰበው ፡ ዝቅተኛ ፡ የሆኑት ፡ የአድሚኒስትራሲዮን ፡ ክፍሎች ፡ ከሚያቀርቡት ፡ ግምት ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ የበጀቱም ፡ ዝርዝር ፡ የዓመቱን ፡ መዛግብት ፡ በመመልከት ፡ ሊገመት ፡ የሚችለውን ፡ መደበኛ ፡ ወጪና ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠበትንና ፡ የሚፈጀው ፡ ዋጋ ፡ የተመዘነውን ፡ የካፒታል ፡ ወጪ ፡ መጨመር ፡ አለበት ። የበጀቱ ፡ ወጪ ፡ አሳብ ፡ ከምክንያቱ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ መጀመሪያ ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከዚያም ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤትና ፡ ለፓርላማ ፡ መተላለፍ ፡ አለበት ።

ስለዚህ ፡ ሚኒስትሮች ፡ የበጀት ፡ ግምታቸውን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ከሚጠይቀው ፡ ደብዳቤ ፡ ጋር ፡ በጀቱ ፡ እንዴት ፡ እንደሚዘጋጅ ፡ የሚያስረዳ ፡ "አንድ ፡ የበጀት ፡ መምሪያ" ተያይዞ ፡ ይላካል ። ይህ ፡ መምሪያ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ። የመጀመሪያው ፡ ስለገቢ ፡ ግምት ፡ ስለወጪ ፡ መጨመር ፡ ማስፈለግ ፡ አለማስፈለጉን ፡ ካስፈለገም ፡ የትኛውን ፡ አቅጣጫ ፡ እንደሚወስድ ፡ የሚያመለክተውን ፡ ጠቅላላ ፡ መምሪያ ፡ የያዘው ፡ የበጀት ፡ ፖሊሲ ፡ ጠቅላላ ፡ መግለጫ ፡ ነው ። ይህ ፡ መምሪያ ፡ ለጊዜው ፡ የሚይዘው ፡ አጠቃላይ ፡ ነጥቦችን ፡ ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ ወደፊት ፡ ተሻሽሎ ፡ በመደበኛና ፡ በካፒታል ፡ ወጪዎች ፡ በኩል ፡ የሚፈቀደውን ፡ የጭማሪ ፡ ልክ ፡ (በመቶ) በዝርዝር ፡ እንዲያሳይ ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መምሪያ ፡ የየሚኒስቴሩ ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡

መስጠት ፡ አለበት ፤ ወይስ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የቀረበለትን ፡ የየሚኒስቴሩን የበጀት ፡ ግምት ፡ በጁ ፡ ካለው ፡ መረጃ ፡ ጋር ፡ እያስተያየ ፡ መመርመር ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ጥያቄ ፡ አለ ። ይህ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ የሚሰጠው ፡ መምሪያ ፡ ወሰን ፡ እንዳለው ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፤ ይህ ፡ መምሪያ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከሚያወጣቸው ፡ የአስተዳደር ፡ ትእዛዝ ፡ ጋር ፡ ይስማማልን ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ አለ ። በፖሊሲ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ ይህ ፡ መምሪያ ፡ ይበልጥ ፡ የሚጠቅመው ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤትን ፡ ነው ።

የመምሪያው ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የሚመለከተው ፡ የበጀቱን ፡ የአቀራረብ ፡ ፎርም ፡ ነው ። ይህ ፡ ክፍል ፡ የበጀቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በበለጠ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሲሄድ ፡ የሚለወጥ ፡ ቢሆንም ፡ አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ ፡ አሁን ፡ የሚሠራበትን ፡ የበጀት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚያሳይ ፡ ስለሆነ ፡ ባጭሩ ፡ መጥቀስ ፡ ያስፈልጋል ። የሚቀርበው ፡ የወደፊት ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ የሚመሠረተው ፡ በአሁኑ ፡ ዓመት ፡ በጀት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ ተጨማሪ ፡ የሆኑ ፡ የተፈቀዱ ፡ ወጪዎች ፡ ከክፍሉ ፡ የተመሩትንና ፡ እንደገና ፡ የተመደቡትን ፡ እንዲሁም ፡ የአሁኑ ፡ ዓመት ፡ በጀት ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ በመሆኑ ፡ የሚደረገውን ፡ ቅናሽ ፡ ሁሉ ፡ ይይዛል ። ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ የአሁኑ ፡ ዓመት ፡ በጀት ፡ "የሚከፈል ፡ መደበኛ ፡ ወጪ" ይባላል ።

የበጀት ፡ ዝርዝር ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ተተንትኖ ፡ መቅረብ፡ አለበት ። የቀረበው ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ ከሚከፈለው ፡ መደበኛ ፡ ወጪ ፡ የበለጠ እንደሆነ ፡ ብልጫው ፡ ተቀባይነትን ፡ የሚያገኝበት ፡ ምክንያት ፡ በጽሑፍ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። በተጨማሪም ፡ በደሞዝና ፡ አበል ፡ ረገድ ፡ በሚኒስቴሩ ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የሥራ ፡ ደረጃ ፡ የተመደበ ፡ የደመወዝ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫና ፡ ለእያንዳንዱም ፡ የሠራተኞች ፡ ጓድ ፡ ማለት ፡ ለአስተዳደር ፡ ሠራተኞች ፡ ለሙያተኞች ፡ ለቴክኒሺያኖች ፡ ለባለልዩ ፡ ሙያ ፡ ሠራተኞች ፡ የውጪ፡ ዜግነት ፡ ላላቸው ፡ ሠራተኞችና ፡ ለወታደርና ፡ ለፖሊስ ፡[11] አጭር ፡ መግለጫ ፡ ተሰናድቶ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። የአርእስቱ ፡ አጫጭር ፡ መግለጫዎች ፡ በጀቱን ፡ ለማጠቃለል ፡ ይረዳሉ ። ዝርዝሩ ፡ መግለጫ ፡ በጀቱን ፡ ለማጽደቅ ፡ አላፊነት ፡ የተሰጣቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የበጀቱን ፡ ግምት ፡ ሲመረምሩ ፡ የሚመለከቱት ፡ ነው ።

የወታደር ፡ ደመወዝና ፡ አበል ፡ በዝርዝር ፡ መቅረብ ፡ ቢኖርበትም ፡ በበጀት ፡ ለሲቪል ፡ ሠራተኞች ፡ እንደሚደረገው ፡ በበጀት ፡ አዋጁ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ አይወጣም ።

የየክፍሉ ፡ በጀት ፡ ወጪው ፡ የሚከፈለው ፡ ከጠቅላላው ፡ ገቢ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሁሉንም ፡ ወጪ ፡ ማጠቃለል ፡ አለበት ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ወጪያቸውን ፡ ከገቢያቸው ፡ እንዲከፍሉ ፡ እንደሚፈቀድላቸው ፡ ሆስፒታሎች ፡ የአንድ ፡ ክፍል ፡ ወጪ ፡ የሚከፈለው ፡ ከውጭ ፡ እርዳታም ፡ ሆነ ፡ ከክፍሉ ፡ ገቢ ፡ በክፍሉ ፡ በጀት ፡ መግባት ፡ አለበት ። በዚሁ ፡ አይነት ፡ የትምህርት ፡ ሚኒስቴርና ፡ የሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከትምህርትና ፡ ከጤና ፡ ታክስ ፡ በሚያገኙት ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፍሉትን ፡ ወጪ ፡ በበጀታቸው ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት ፡ አለ

11. ይህ ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የቀረበ ፡ ጊዜያዊ ፡ አመዳደብ ፡ ነው ።

ባቸው ።[12] ይህ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የበጀቱ ፡ ግምት ፡ ጠቅላላውን ፡ የወጪ ፡ ግምት ፡ ማሳየት ፡ ስላለበት ፡ ነው ። የተባሉት ፡ ገቢዎች ፡ በገቢ ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ።

በካፒታል ፡ ወጪ ፡ ውስጥ ፡ አዳዲስ ፡ ፕሮግራሞችን ፡ የሚመለከት ፡ የወጪ ፡ ግምት ፡ ከፕሮግራሞቹ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ጋር ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ይህ ፡ መግለጫ ፡ በበጀት ፡ ዘመኑ ፡ ውስጥ ፡ ሊደረግ ፡ የታሰበውን ፡ ወጪ ፡ እንዲያሳይ ፡ ያስፈልጋል ። ቀደም ፡ ብለው ፡ በተቋቋሙና ፡ በበጀት ፡ ዘመኑ ፡ ውስጥ ፡ ይፈጸማሉ ፡ ተብለው ፡ በማይጠበቁት ፡ ፕሮግራሞች ፡ ላይ ፡ የሚደረገውም ፡ ወጪ ፡ ከበጀት ፡ ግምቱ ፡ ጋር ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

የገቢ ፡ ግምት ።

ሚኒስቴሮች ፡ መደበኛና ፡ የካፒታል ፡ ወጪ ፡ ግምታቸውን ፡ በሚያዘጋጁበት ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የገቢ ፡ ግምትን ፡ ያዘጋጃል ። የገቢው ፡ ግምት ፡ ለማስተያየት ፡ ያህል ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ የተገኘውን ፡ ትክክለኛ ገቢ ፡ በተያዘው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ፡ ተብሎ ፡ የሚታሰበውን ፡ የገቢ ፡ ልክና ፡ የበጀት ፡ ዓመቱን ፡ ግምት ፡ ያሳያል ። የገቢው ፡ ግምት ፡ ሲዘጋጅ ፡ ያለፉት ፡ ዓመታትን ፡ የገቢ ፡ ልክ ፡ የታክስ ፡ ልክ ፡ በመለወጡ ፡ የሚከተለውን ፡ ውጤት ፡ የአዲስ ፡ ታክስ ፡ መጨመርንና ፡ ምህረት ፡ መደረጉን ፡ የታክስ ፡ አስተዳደር ፡ መሻሻልን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጉዳዮችን ፡ ማስታወስ ፡ አስፈላጊ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ለጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ ሲባል ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ንግድ ፡ ጠቅላላ ፡ አዝማሚያ ይጠናል ።

ቀጥተኛና ፡ ቀጥተኛ ፡ ያልሆነ ፡ ታክስና ፡ የጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ ሦስቱን ፡ የመጀመሪያ ፡ መደበኛ ፡ የገቢ ፡ አርእስት ፡ ይይዛሉ ። በአራተኛና ፡ በአምስተኛ፡ የገቢ ፡ አርእስት ፡ ስር፡የሚመደቡት፡ ከፍርድ ፡ ቤቶችና፡ከሌሎችየመንግሥት፡መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙት ፡ ገቢዎች ፡ የሚገመቱትና ፡ የሚቀርቡት ፡ በተመሳሳይ መንገድና ፡ ፎርም ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ገቢ ፡ የሚያገኙት ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ የገቢ ፡ ግምታቸውን ፡ ከወጪ ፡ ግምታቸው ፡ ጋር ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ይጠየቃሉ ።

ከመንግሥት ፡ ንብረትና ፡ መንግሥት ፡ ከሚያሠራበት ፡ ካፒታል ፡ (ኢንቨስትሜንት) ፡ የሚገኘው ፡ ፮ኛው ፡ መደበኛ ፡ የገቢ ፡ አርእስት ፡ የሚገመተው ፡ በዘመኑ ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ መሠረት ፡ ሲሆን ፡ በበጀት ፡ ዘመኑ ፡ ውስጥ ፡ ገቢውን ፡ ሊቀንሱ ፡ ወይም ፡ ሊጨምሩ ፡ የሚችሉ ፡ ነገሮች ፡ ይታሰብባቸዋል ። ከኢንቨስትመንት ፡ የሚገኘውን ፡ ገቢ ፡ ለመገመት ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ ሂሣቦች ፡ ብዙ ፡ መረጃዎች ፡ ለማግኘት ፡ ይቻላል ።

---

12. የጤናና ፡ የትምህርት ፡ ታክሶች ፡ የወጡት ፡ በድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፴፮ ፡ ፲፱፻፵፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አስራ ፡ ስምንተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፬ ፡ እና ፡ በአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ሰባተኛ፡ዓመት ፡ ቁጥር ፫ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ታክሶች ፡ የሚቆጠሩት ፡ እንደ ፡ መደበኛ ፡ የመሬት፡ ግብር ፡ ክፍል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከታክሶች ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ የሚወጣው ፡ ለጤናና፡ለትምህርት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከጤና ፡ ታክስ ፡ የሚገኘው፡ ገንዘብ ፡ የሚወጣበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚወስነው ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አሥራ ፡ ዘጠነኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ፡ ሲሆን ፡ ከትምህርት ፡ ታክስ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ የሚወጣበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚወስነው ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፺፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ነው ።

በመጨረሻም ፡ ከውጪ ፡ አገሮች ፡ የሚገኘው ፡ እርዳታ ፡ የሚደመረው ፡ ጠቅላላውን ፡ የመንግሥት ፡ መደበኛ ፡ ገቢ ፡ ለማወቅ ፡ እንዲመች ፡ ነው ።

## የበጀት ፡ መቀነባበር ።

ሚኒስቴሮችና ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ የበጀት ፡ ዝግጅታቸውን ፡ ፈጽመው ፡ የበጀቱን ፡ ግምት ፡ መስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር፡መላክ ፡ አለባቸው።ይህ ፡ ከየሚኒስቴሩና፡ከየመንግሥት፡ድርጅቱ፡የተላከው፡የበጀት ፡ ግምት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ወደሚቀነባበርበት ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ይተላለፋል ።

የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ የቀረበው ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ የሚከተሉትን ፡ ተፈላጊ ፡ ነጥቦች ፡ መያዙን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

— የሚያስፈልጉ ፡ ሃሳቦች ፡ መኖራቸውን ፤
— ግምቱ ፡ ለመቀነባበርና ፡ ለመጠናት ፡ ዝግጁ ፡ መሆኑን ፤
— የተሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ለተጠየቀው ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ ቀጥታ ፡ ማስረጃ ፡ መሆኑንና ፡ የበጀት ፡ ጠቅላላ ፡ መግለጫ ፡ አለመሆኑን ።

በኋላ ፡ ችግር ፡ ከሚፈጥር ፤ በቂ ፡ ያልሆነውን ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ ሁሉ ፡ ለላከው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ መመለስ ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የሚደረገው ፡ የሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ ሁኔታዎች ፡ የተገኙ ፡ እንደሆነ ነው፡— ፩ኛ ፡ የበጀቱ ፡ ግምት ፡ በጊዜ ፡ ቀርቦ ፡ እንደሆነ ፡ ፪ኛ/ የበጀት ፡ ማደራጃ፡ ዲሬክሲዮን ፡ በየሚኒስቴሩና ፡ በየመንግሥት ፡ ድርጅቱ ፡ ከሚገኙ ፡ ለቀረቡት ፡ የበጀት ፡ ግምቶች ፡ አላፊ ፡ ከሆኑ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋር ፡ የተጨበጠ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ እንደሆነና ፤ ፫ኛ/ የዲሬክሲዮኑ ፡ ባለሥልጣኖች ፤ ሚኒስቴሮችንና፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶችን ፡ በቅርብ ፡ ያውቋቸው ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። የመጀመሪያው ፡ ሁኔታ ፡ ማለት ፡ የበጀቱን ፡ ግምት ፡ በጊዜ ፡ ማቅረብ ፡ ለመፈጸም ፡ ጭራሽ ፡ የሚቻል ፡ አይመስልም ፤ የሚከተሉት ፡ ሁለቱ ፡ ሁኔታዎች ፡ አሁን ፡ ባለው የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ድርጅት ፡ የተነሳ ፡ ሊፈጸሙ ፡ አልቻሉም ።[13]

የበጀት ፡ ማደራጃው ፡ ዲሬክሲዮን ፡ የአለፈውን ፡ ዘመን ፡ አሁን ፡ የሚሠራበትንና ፡ ለመጪው ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ የቀረበውን ፡ ወጪ ፡ ከየሚኒስቴሩና፡ ከየመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በተገኘው ፡ የበጀት ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ በሠንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ አስገብቶ ፡ ያስተያያል ። በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ የሚደረገው ፡ የበጀት ፡ ዝግጅት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሲፈጸም ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚያቀርበው ፡ ግምትም ፡ በሠንጠረዡ ፡ ውስጥ ፡ ይመለከታል ።

## የመጀመሪያው ፡ የበጀት ፡ ረቂቅ ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ በሠንጠረዦቹ ፡ መሠረት ፡ የመጀመሪያውን ፡ የበጀት ፡ ረቂቅ ፡ የማዘጋጀቱን ፡ ተግባር ፡ ለአንድ ፡ የበጀት ፡ ኮሚቴ ፡ ሰጥቷል ።

---

13. በበጀት ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ውስጥ ፡ የበጀቱን ፡ ሂሣቦች ፡ ከፋፍሎ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ አንዳንድ ፡ ተቆጣጣሪ ፡ መመደብ ፡ ጥሩ ፡ ዘዴ ፡ ይመስላል ። እያንዳንዱ ፡ ተቆጣጣሪ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የተመደቡትን ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ መ/ቤቶች ፡ በቅርብ ፡ ለመከታተል ፡ ከመቻሉም ፡ በላይ ፡ በመጀመሪያ ፡ በመ/ቤቶች ፡ ከሚዘጋጁት ፡ ሂሣቦችና ፡ በመጨረሻ ፡ ከሚደረገው ፡ የበጀት ፡ መቀነባበር ፡ በስተቀር ፡ ለበጀት ፡ ቊጥሮች ፡ ዝግጅት ፡ ሃላፊ ፡ ይሆናል ።

ኮሚቴው ፡ የሚመራው ፡ የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ኃላፊ ፡ በሆነው ፡ ረዳት ፡ ሚኒስትር ፡ ሆኖ ፡ የፕላኒንግ ፡ ቦርድን ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የክሬዲትና ፡ የፊናንስ ፡ ዲሬክሲዮንን ፡ እንዲሁም ፡ የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮንን ፡ የሚወክሉ ፡ ሹማምንቶችና ፡ የፊናንስ ፡ የኤኮኖሚና ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ አዋቂዎች ፡ ይገኙበታል ።

ኮሚቴው ፡ የወጪ ፡ ግምቱን ፡ ሲያጠና ፡ ከሚመለከታቸው ፡ ነጥቦች ፡ አንዳንዶቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፦

- ፩ ፤ የበጀቱ ፡ ግምት ፡ ከገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በተላከው ፡ መምሪያ ፡ መሠረት ፡ መዘጋጀቱን ፤
- ፪ ፤ የበጀቱ ፡ ግምት ፡ የገቢውን ፡ ጣራ ፡ መጠበቁን ፤
- ፫ ፤ በጀቱ ፡ መጠኑን ፡ እንዳይዘልና ፡ የማይሠራበትን ፡ ወጪ ፡ እንዳይዝ ፤
- ፬ ፤ የወጪው ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ፕላን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ መቻሉን ፡ (ለምሳሌ ፡ የአስተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ እንዲያድግ ፡ የቀረበው ፡ ሃሳብ ፡ አስተማሪዎቹ ፡ የሚመለመሉላቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ባይሠሩ ፡ እንኳን ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን) ፤
- ፭ ፤ በብሔራዊው ፡ መምሪያ ፡ (ፖሊሲ) ረገድ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ሚኒስቴር ፡ ፕሮግራሞች ፡ የሚሰጠውን ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ ደረጃ ፤
- ፮ ፤ የቀረበው ፡ የካፒታል ፡ ወጪ ፡ ግምት ፡ ከመንግሥቱ ፡ የልማት ፡ መምሪያ ፡ (ፖሊሲ) ጋር ፡ ተስማሚ ፡ መሆኑን ።

ኮሚቴው ፡ የአቅራቢው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወኪሎች ፡ ቀርበው ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያ ፡ እንዲሰጡ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። የኮሚቴው ፡ ውይይት ፡ የተሰጡትን ፡ አስተያየቶች ፡ በሰፊው ፡ በመጥቀስ ፡ በዝርዝር ፡ ይጻፋል ።

<u>የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አሳብ ።</u>

የበጀት ፡ ኮሚቴው ፡ አስተያየት ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሲቀርብ ፡ የበጀቱን ፡ ረቂቅ ፡ የሚመለከት ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥበታል ። ይህ ፡ ረቂቅ ፡ የኤኮኖሚና ፡ የፊናንስ ፡ ጉዳዮችን ፡ ከሚመለከተው ፡ ከሚኒስትሩ ፡ አስተያየት ፡ ጋር ፡ ከታህሣሥ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይተላለፋል።

### የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጀቱን ፡ ስለማጥናቱ

የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጀቱን ፡ በጠቅላላ ፡ ሁኔታ ፡ ከተነጋገረበት ፡ በኋላ ፡ ለዝርዝር ፡ ጥናት ፡ ወደ ፡ በጀት ፡ ኮሚቴው ፡ ያስተላልፋል ። ኮሚቴው ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚመረጡ ፡ ሰባት ፡ አባሎች ፡ ይገኙበታል ።[14] ይህ ፡ ኮሚቴ ፡ የበጀት ፡ ግምቱን ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሚኒስትሮች ፡ በሚያቀርቡት ፡ ጽሑፎችና ፡ እንዲያቀርቡ ፡ የተጠየቁት ፡ የየሚኒስቴሩ ፡ ወኪሎች ፡ በሚሠጡት ፡ ማብራሪያ ፡ መሠረት ፡ ያጠናል ። የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ፡ እራሱ ፡ ከመገኘቱም ፡ በላይ ፡ እነዚህ ፡ ማብራሪያዎች ፡ በሚሰሙበት ፡ ጊዜ ፡

14. አንዳንዶቹ ፡ የኮሚቴው ፡ አባሎች ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ አይደሉም ።

ሁሉ ፡ በኮሚቴው ፡ ላይ ፡ በሚኒስቴሩ ፡ የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ አላፊ ፡ ይወከላል ።

ከጥናቱ ፡ በኋላ ፡ የበጀት ፡ ግምቱ ፡ ከኮሚቴው ፡ አስተያየትና ፡ ማሻሻያዎች ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ። በዚሀ ፡ ጊዜ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለፓርላማ ፡ ስለሚቀርበው ፡ የበጀት ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ በሚኒስቴሩ ፡ የተዘጋጀውን ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ ከሚኒስቴሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ማሻሻያዎች ፡ ጋር ፡ ማስተካከል ፡ አለበት ። የሚኒስትሮቹ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ለበጀት ፡ ማደራጃው ፡ ዲሬክሲዮንና ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በአስቸኳይ ፡ መላክ ፡ አለባቸው ። ውሳኔዎቹ ፡ ከተለዩ ፡ የበጀቱ ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ እንዲዛመዱና ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ ለውጦች ፡ እጥር ፡ ምጥን ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲገልጹ ፡ ያስፈልጋል ። ይህ ፡ የሚደረገው ፤ ለውጦቹ ፡ ከበጀቱ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ ያለባቸው ፡ ጊዜ ፡ ዘግየት ፡ ያለ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በተጨማሪም ፤ በበጀቱ ፡ ውስጥ ባሉት ፡ አዛማጅ ፡ ሐረጐች ፡ መወሳሰብ ፡ ምክንያት ፡ አነስተኛው ፡ ለውጥ ፡ እንኳን ፡ የበጀቱን ፡ ግምት ፡ ስለሚያቃውስ ፡ ነው ።

## <u>ፓርላማው ፡ በጀቱን ፡ ስለማጥናቱ።</u>

### <u>የፓርላማው ፡ ተግባር</u> ።

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፲፭ ፡ መሠረት ፡ የበጀት ፡ ግምቱ ፡ ከመጋቢት ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይቀርባል ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲያጸድቀው ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አማካይነት ፡ ለፓርላማው ፡ ይቀርባል ።

የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ፡ "ማናቸውም ፡ የመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ በሕግ ፡ እንደተፈቀደው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወጪ ፡ አይሆንም ፤" ይላል ተከታዮቹ ፡ አንቀጾች ፡ ደግሞ ፡ "ሕግ" የሚለው ፡ ቃል ፡ "ፓርላማ ፡ ያወጣው ፡ ሕግ" መሆኑን ፡ ያመለክታሉ ። ይሀ ፡ ለፓርላማ ፡ የተሰጠው ፡ በጀትን ፡ የመቆጣጠር ፡ ጠቅላላ ፡ ሥልጣን ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። አንደኛ ፤ በአንቀጽ ፡ ፻፲፯ ፡ መሠረት ፡ ፓርላማው ፡ ከቀረበለት ፡ ረቂቅ ፡ በጀት ፡ ውስጥ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ወጪ ፡ በላይ ፡ ለመፍቀድ ፡ አይችልም ። ቢሆንም ፡ ፓርላማው ፡ ለአንድ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ዝርዝር ፡ የተመደበውን ፡ ወጪ ፡ ከመጨመር ፡ አይታገድም ። ነገር ፡ ግን ፤ የበጀቱ ፡ ሚዛን ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለአንድ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ዝርዝር ፡ የተመደበው ፡ ወጪ ፡ ሲጨመር ፡ በበጀቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሌላ ፡ ጉዳይ ፡ የተመደበው ፡ ወጪ ፡ መቀነስ ፡ አለበት ።

ሁለተኛው ፡ ወሰን ፡ የሚፈጠረው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፯ንና ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ን ፡ በማጣመር ፡ ነው ። በመጀመሪያው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ በጀት ፡ በአዲሱ ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ካልወጣ ፡ የአለ

ፈው ፡ ዘመን ፡ በጀት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይውላል ።[15] በሁለተኛው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ በፓርላማ ፡ ያለፈ ፡ ውሳኔ ፡ (ያመት ፡ በጀት ፡ ጭምር) ሕግ ሆኖ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መጽደቅ ፡ አለበት ። ሁለቱ ፡ አንቀጾች ፡ ሲጣመሩ ፡ መንግሥቱ ፡ ሳልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ያለፓርላማ ፡ የበጀት ፡ ቁጥጥር ፡ ሊካሄድ ፡ መቻሉን ፡ ያመለክታሉ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፓርላማው ፡ ያሳለፈውን ፡ ውሳኔ ፡ ካላጸደቀው ፡ ባለፈው ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ የወጣው ፡ የበጀት ፡ አዋጅ ፡ ለመንግሥት ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥት ፡ ፍላጐቶች ፡ መብዛት ፡ ይህ ንን ፡ ሁለተኛውን ፡ የሕግ ፡ ወሰን ፡ ክብደት ፡ አይሰጠውም ።[16]

## <u>የበጀት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በፓርላማ ፡</u>

ለፓርላማ ፡ የሚቀርበው ፡ ረቂቅ ፡ ስለእያንዳንዱ ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ከሌለም ፡ ስለእያንዳንዱ ፡ የተራ ፡ ወጪ ፡ አርእስት ፡ የተጻፉትን ፡ መግለጫዎች ፡ ይጨምራል ። መግለጫዎቹ ፡ የሚሰጡት ፡ የሚከተሉትን ፡ ነው።

፩ ፤ ለደመወዝ ፡ (የሲቪል ፡ ደመወዝ ፡ የሲቪልና ፡ የመኪና ፡ አበል ፤ የወታደርና ፡ የፖሊስ ፡ ደመወዝና ፡ አበል) ፡ የሥራ ፡ ቦታዎች ፡ ቍጥር ፤ የደመወዝ ፡ መጠን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የሥራ ፡ ቡድን ፡ የሚደረገው ፡ የወር ፡ ወጪ ፡ ድምርና ፡ የዓመቱ ፡ ወጪ ፡ ድምር፡ ለሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ ቡድኖች ፡ የአስተዳደር ፡ ሠራተኞች ፡ የቴክኒክና ፡ የሙያ ፡ ሠራተኞችና ፡ የውጪ ፡ ዜግነት ፡ ያላቸው ፡ ሠራተኞች ፤

፪፤ በቀሩት ፡ የተራ ፡ ወጪዎች ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ዝርዝሮች ፡ (ተሽከርካሪዎች ፡ መሣሪያዎችና ፡ በየጊዜው ፡ የሚቀርቡ ፡ ዕቃ ዎች ፡ ሌሎች ፡ ወጪዎች) ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ንዑስ ፡ የወጪ ፡ ክ ፍል ፡ የተመደበው ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ ይገለጻል ("መሣሪያ ዎች" በሚለው ፡ ሥር ፡ ፲፩ ፡ የሚደርሱ ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ሲኖሩ ፡ "ሌሎች ፡ ወጪዎች" በሚለው ፡ ደግሞ ፡ ፲፱ ፡ የሚደ ርሱ ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ አሉ) ።

በአንቀጽ ፡ ፹፯ ፡ መሠረት ፡ "ማንኛውም ፡ የወጪ ፡ በጀት ፡ ጭማሪ ፡ ጉዳይ ፡ በቀደምት ፡ ለሕገ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት፡ መቅረብ ፡ ያለበት ከመሆኑ ፡ በስተቀር ፡ ፓርላማው ፡ ይህን ፡ ረቂቅ ፡ የሚመክርበት ፡ ልክ ፡

---

15. ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ የፓርላማውን ሥልጣን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ያጠነከረው ፡ ይሆናል ። ንጉሠ ፡ ነገ ሥቱ ፡ "አማካሪዎች ፡ ባልተሰበሰቡበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቸኩል ፡ ጉዳይ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ" እስፓርላማው ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ ያልተወሰነ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መን ግሥት ፡ ቍጥር ፡ ፺፪ ። በበጀት ፡ ሕግ ፡ በኩል አንቀጽ ፡ ፻፲፮ ፡ ማንኛውንም ፡ ሌላ ፡ "አስቸ ኳይ" ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ስለማይጨምር ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አግባብ ፡ የለውም ፡ ማለት አከራካሪ ፡ ነው ።

16. ይህ ፡ አስተያየት እስ ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ በሚቻለው ፡ በአንድ ፡ ሌላ ፡ የሕግ ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት፡ሊኖረው፡ይችላል፤ይሀም ፡ ፓርላማው ፡ የበጀት ፡ ማውጣት ፡ ሥልጣኑን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከማዋሉ ፡ በፊት ፡ ረቂቅ ፡ በጀቱን ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

እንደሌላው ፡ ሕግ ፡ ነው ። [17] የሚቀርበው ፡ በጀት ፡ ከአለፈው ፡ ዘመን ፡ በጀት ፡ የበለጠ ፡ ስለሚሆን ፡ በቀደምት ፡ ለሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡የተለመደ ፡ ሆኗል ።

የሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የበጀቱን ፡ ረቂቅ ፡ የሚመረምር ፡ አንድ ፡ ቀዋሚ ፡ የበጀት ፡ ኮሚቴ ፡ አለው ። ኮሚቴው ፡ የአስተዳደሩን ፡ ክፍል ፡ የሚወክሉ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ የበጀት ፡ አቤቱታ ፡ ይሰማል ። አሁን ፡ እንደሚደረገው ፡ አቤቱታው ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ በኮሚቴው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ወኪል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሌሎች ፡ ሚኒስትሮችና ፡ ድርጅቶች ፡ አባሎችም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በኮሚቴው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ የበጀት ፡ ግምታቸውን ፡ የሚደግፍ ፡ ማብራሪያ ፡ ቢሰጡ ፡ የተሻለ ፡ ነው ።

የበጀት ፡ ኮሚቴው ፡ መግለጫውን ፡ ለሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሲያቀርብ ፡ ድምጽ ፡ የሚሰጠው ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፮ ፡ መሠረት ፡ በያንዳንዱ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ ነው ። በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ሚኒስትር ፡ ዴኤታ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሥነ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ እየተገኘ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያቀረበውን ፡ ግምት ፡ የሚመለከቱ ፡ ጥያቄዎችን ፡ ይመልሳል ። በጀቱ ፡ መጽደቅ ፡ ያለበት ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ነው ።[18] ነገር ፡ ግን ፡ ምልዓተ ፡ ጉባኤ ፡ ሳይኖር ፡ ድምጽ ፡ አይሰጥም ።[19]

በጀቱን የሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከተቀበለው ፡ በኋላ ፡ በክፍሉ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በኩል ፡ ለሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይተላለፋል ። የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጀቱን ፡ በሚያጠናበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከተለው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር፡ ይመሳሰላል ። የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጀቱን ፡ አጥንቶ ፡ ራፖር ፡ የሚያቀርብለት ፡ ኮሚቴ ፡ ይመርጣል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የድምጽ ፡ መስጠቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሕግ ፡ መምሪያው ፡ የድምጽ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

## በጀቱን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማቅረብ ፡ የሁለቱ ፡ ምክር፡ቤቶች፡አለመስማማት።

የሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያሳለፈውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳያሻሽል ፡ የተቀበለው ፡እንደሆነ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አማካይነት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀርቦ፡ ሲፈቀድ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ። ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሕግ ፡ አሳቡ ፡ ላይ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ ጨምሮ ፡ ወደ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ መልሶ ፡ ይልከዋል ። [20] ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ ሥልጣን ፡ ግን ፡ እምብዛም ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም ።

17. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፓርላማ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማብራሪያ ፡ ለማግኘት ፡ በኬ ፡ ሬደን ፡ የተጻፈውን ዘ ፡ ሎው ፡ ሜኪንግ ፡ ፕሮሰስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ) የተባለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ይመለከቷል ።
18. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፹፮ ።
19. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፸፱ ።
20. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የማይስማሙበት ፡ ጊዜ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። የምክር ፡ ቤቶቹ ፡ የአሳብ ፡ ግጭት ፡ ከሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ ሁናቴዎች ፡ የአንዱን ፡ መልክ ፡ ይይዛል ። አንደኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በተቀበለው ፡ የበጀት ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ሁለተኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በተባለው ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ውሳኔ ፡ ሳያደርግ ፡ ይቀር ፡ ይሆናል ፤ ምናልባት ፡ ሁለተኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የበጀት ፡ አሳቡን ፡ አሻሽሎ ፡ ይቀበለዋል ፤ ወይም ፡ አሳቡን ፡ ሳይቀበለው ፡ ይቀራል ። የሁለቱን ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ በሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ላይ ፡ አለመስማማት ፡ የሚመለከቱ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ ይፈጸማሉ ።

ሁለተኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በበጀት ፡ አሳቡ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ ካልሰጠ ፡ ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፱ ፡ መሠረት ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይሰበሰባሉ ። ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ በሚያደርጉት ፡ ስብሰባ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ አሳቡን ፡ የተቀበሉት ፡ እንደሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ብቻውን ፡ እንደተቀበለው ፡ ተቆጥሮ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይላካል ።

የአንቀጽ ፡ ፺ና ፡ አንቀጽ ፡ ፺፩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በቀሩት ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ይፈጸማሉ ። በአንቀጽ ፡ ፹፱ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈው ፡ የአንድነት ፡ ስብሰባ ፡ የሕግ ፡ አሳቡን ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፺፩ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል።

## አንቀጽ ፡ ፺ ።

“አንደኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የተቀበለውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ ሁለተኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ አሻሽሎ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ የተባለው ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ እንደገና ፡ እስተያየት ፡ እንዲደረግበት ፡ ለመጀመሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተመልሶ ፡ ይላካል ። እስተያየት ፡ እንዲደረግበት ፡ የተመለሰለትን ፡ አሳብ ፡ የመጀመሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ከነማሻሻያዎቹ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆን ፡ ፹፰ኛው ፡ አንቀጽ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ እንዲሠራበት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይላካል ። የመጀመሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እነዚህን ፡ ማሻሻያዎች ፡ ያልተቀበላቸው ፡ እንደሆነ ፡ በዚሁ ፡ አሳብ ፡ ለመነጋገር ፡ ምክር ፡ ቤቶቹ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ስብሰባ ፡ ያደርጋሉ ። ምክር ፡ ቤቶቹ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ስብሰባ ፡ ተሻሽሎም ፡ ሆነ ፡ ሳይሻሻል ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በአሳቡ ፡ የተስማሙበት ፡ እንደሆነ ፡ በ፹፰ኛው ፡ አንቀጽ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ እንዲሠራበት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይላካል ።”

## አንቀጽ ፡ ፺፩ ።

“በአንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ እንደተመለከተው ፡ አንደኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የተቀበለውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ ሁለተኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ከተላለፈለት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፱ና ፡ ፺ ፡ መሠረት ፡ ሁለቱም ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ንግግር ፡ ካደረጉበት ፡ በኋላ ፡ ተሻሽሎም ፡ ሆነ ፡ ሳይሻሻል ፡ በሕጉ ፡ አሳብ ፡ ሳይስማሙበት ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ የፓርላሜንቱ ፡ የሁለቱም ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ፕሬዚዳንቶች ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳይ ፡ ሙሉ

ራፖር ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ በኩል ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በፍጥነት ፡ ይልካሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ራፖሩን ፡ መልሶ ፡ ከአስተያየቱ ፡ ጋር ፡ ለሁለቱም ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ይልከዋል ፤ ወይም ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለምክር ፡ ቤቶች ፡ እንዲተላለፍላቸው ፡ ይደረጋል ።"

## የበጀት ፡ አከፋፈልና ፡ ቊጥጥር ።

በጀቱ ፡ ጸድቆ ፡ እንደወጣ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዝርዝር ፡ በጀቱን ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያስተላልፋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በጀታቸውን ፡ በአርእስት ፡ ወይም ፡ በወጪ ፡ ዝርዝር ፡ እንደገና፡ለማደላደል ፡ የሚፈልጉ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ በበጀት ፡ አዋጅ ፡ እንደተደነገገው ፡ ከገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማስፈቀድ ፡ አለባቸው ።[21] በአሠራር ፡ ልማድ ፡ ይህን ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ የሚኒስቴሩ ፡ የበጀት ፡ ማደራጃ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ነው ።

የበጀቱ ፡ ዝርዝር ፡ በተጨማሪ ፡ የበጀቱን ፡ ቊጥጥር ፡ ለሚያካሂደው ፡ ለበጀት ፡ ክፍያ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ይላካል ።

## የበጀት ፡ አመዳደብ ።

የበጀት ፡ ቁጥጥሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ሊጠቃለል ፡ ይችላል ።

፩ ፤ የበጀት ፡ ክፍያው ፡ ዲሬክሲዮን ፡ የያንዳንዱን ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ሒሣብ ፡ ይመዘግባል ።

፪ ፤ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሒሣብ ፡ የሚያዘው ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በሚገኘው ፡ በጅሮንድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ነው ። ዝርዝሩ ፡ የሚላከው ፡ ግን ፡ ከበጀት ፡ ማደራጃው ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ወጪዎችን ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ለበጅሮንዶቹ ፡ ተሰጥቷል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፫ ፤ ከጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ወጪዎች ፡ ሌላ ፡ የበጀት ፡ መደብ ፡ ጥያቄ ፡ የሚቀርበው ፡ ለበጀት ፡ ክፍያ ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ነው ። የበጀት ፡ መደብ ፡ የተፈቀደ ፡ የበጀት ፡ ወጪ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ሲሆን ፡ ዲሬክሲዮኑ ፡ ለከፊል ፡ ዓመት ፡ (አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለአንድ ፡ ወር) ለመደበኛ ፡ ወጪው ፡ ወይም ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ ለሚደረጉ ፡ ከበድ ፡ ያሉ ፡ ወጪዎችን ፡ ለሚጠይቁ ፡ የዕቃ ፡ ግዢና ፡ የካፒታል ፡ ወጪ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሒሳብ ፡ ነው ። የሒሣቡ ፡ መመደብ ፡ የገንዘብን ፡ መክፈል ፡ አያሳይም ። እንደዚህ ፡ ያለው፡ አሠራር ፡ ከጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ መመደብ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የወር ፡ የገንዘብ ፡ ሁኔታ ፡ መግለጫ ፡ ውስጥ ፡ በቀደም ፡ እንደተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ ተቆጥሮ ፡ ይገባል ።

---

21. የበጀት ፡ አዋጆች ፡ የወጡት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ የዚህ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በገጽ ፡ 354 ፡ የተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ፡ ነው ።

፱ ፤ የመደብ ፡ መጠየቂያው ፡ ከተመዘገበው ፡ የበጀት ፡ ሂሣብ ፡ ጋር፡ ሲመሳከር ፡ ደመወዝ ፡ መክፈያው ፡ ካለፈው ፡ ወር ፡ የክፍያ ፡ ደረሰኝ ፡ ጋር ፡ ይመሳከራል ። በተጨማሪም ፡ የሚከተሉት ፡ ነጥ ቦች ፡ መፈጸማቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ ያስፈልጋል ።

— ፈራሚው ፡ ባለሥልጣን ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ አለማለፉ ፤
— የተጠየቁት ፡ ወጪዎች ፡ በበጀቱ ፡ አርእስቶች ፡ ውስጥ ፡ መ መልከታቸውን ፤
— የተጠየቀው ፡ ሂሳብ ፡ በተፈቀደው ፡ በጀት ውስጥ ፡ መመልከቱንና ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ድምር፡ ከበጀት ፡ ማደ ራጃው ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ጋር ፡ መመሳሰሉን ፤
— የደመወዝ ፡ መክፈያው ፡ በዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ በተዘጋ ጀው ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ በተፈቀደው ፡ የደመወዝ ፡ ዝርዝር ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ።

፲ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሌላ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ስም ፡ ለፎኘ ፡ ወገን ፡ ይከፍላል ። ይህ ፡ ወጪ ፡ በተባለው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡እንደተከፈለ፡ወጪ ተቆጥሮ፡ይመዘገ ባል ። ለተለዩ ፡ ድርጅቶች ፡ የሚደረግ ፡ ስጦታ ፡ ለአውራ ፡ ጐዳ ና ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚከፈለው ፡ ሂሣብና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰ ሉት ፡ ክፍያዎች ፡ የሚፈጹሙት ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ነው ።

<u>የክፍያዎችና ፡ የደረሰኞች ፡ መሠረተ ፡ አሳብና ፡ የድንገተኛ ፡ ወጪዎች ፡ መጠ ባበቂያ ።</u>

የኢትዮጵያ ፡ የበጀት ፡ ቅንጅት ፡ በ"ጥሬ ፡ ገንዘብ" ወይም ፡ በ"ክፍያዎ ችና ፡ ደረሰኞች" ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። በጀቱ ፡ የሚሰጠው ፡ ገንዘቦችን ፡ የመክፈል ፡ ሥልጣን ፡ የሚያገለግለው ፡ በበጀት ፡ ዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚደረጉ ትን ፡ ክፍያዎች ፡ ለመፍቀድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከተከታዩ ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ በፊት፡ ያልተደረገ ፡ ክፍያ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ያለፈውን ፡ ዓመት ፡ ግዴታዎች ፡ ለመፈ ጸም ፡ ቢደረግ ፡ በተከታዩ ፡ ዓመት ፡ በጀት ፡ ውስጥ ፡ መፈቀድ ፡ አለበት ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተጻፈው ፡ ደንብ ፡ የተለየ ፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ አለ ። ባለፈው ዓመት ፡ የደረሰ ውን ዕዳ ፡ በተመሳሳይ ፡ አርእስት ፡ ወይም ፡ ንዑስ ፡ አርእስት ፡ ሥር ፡ በማስገባት ፡ በተያዘው ፡ የበጀት ፡ ዘመን ፡ ከተፈቀደው ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ፡ ለመክፈል ፡ ካልተቻለ ፡ ከ"ድንገተኛ ፡ ወጪዎች" ይከፈላል ። ከድንገተኛ ፡ ወጪዎች ፡ መጠባበቂያ ፡ ክፍያዎችን ፡ ማድረግ ፡ በበጀት ፡ አዋጁ ፡ መሠረት ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ።[22]

በአሁኑ ፡ የበጀት ፡ አሠራር ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ መጠባበቂያ ፡ ተጨማሪ ፡ በጀት ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ የሚደረገው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትእዛዝ ፡ የጽሕ ፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ በሚያወጣው ፡ ማዘዣ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ማዘዣው ፡ የሚወ ጣው ፡ በዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ በኩል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ በማዋየት ፡ ነው ። ይህ ፡

22. አዋጁ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ስለወጣ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የተመሠረተው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በገጽ ፡ 354 በተጠቀሰው ፡ በአዋጁ ፡ ፯ ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ ነው ።

ፈቃድ ፡ ከድንገተኛ ፡ ወጪዎች ፡ ዝውውር ፡ ማድረግን ፡ ስለሚጠይቅ ፡ ለሚኒስቴሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ያስፈልጋል ። ተጨማሪ ፡ በጀት ፡ ካለ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሥር ፡ ይመደባል ።

በአሁኑ ፡ የበጀት ፡ አጻምና ፡ ቁጥጥር ፡ መሠረት ፡ ድንገተኛ ፡ ወጪ ፡ ተብሎ ፡ የሚያዝ ፡ ወጪ ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጉዳዩ ፡ ወደሚመለከተው አርእስት ፡ ዝውውር ፡ መደረግ ፡ አለበት ። ይህም ፡ የድንገተኛ ፡ ወጪዎችን ፡ ድምር፡ቀንሶ ፡ ዝውውር፡የተደረገለትን፡አርእስት፡ሂሣብ፡ይጨምራል። ወጪው፡አዲስ ፡ በመሆኑ ፡ የበጀት ፡ ሂሳብ ፡ ቁጥር ፡ ከሌለው ፡ አዲስ ፡ የሂሳብ ፡ ቁጥር ፡ ይከፈትለታል ።

## <u>የበጀት ፡ ዘመኑን ፡ ሂሳብ ፡ መዝጋት ።</u>

የበጀቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ የበጀት ፡ ዘመኑ ፡ ሂሳብ ፡ መዝጊያው ፡ ነው ። የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሂሣብ ፡ ጠቅላይ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የዓመቱን ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ የሚያሳይ ፡ መግለጫ ፡ ያዘጋጃል ። ይህ ፡ መግለጫ ፡ ከሂሳብ ፡ መዝገቦች ፡ የተገኙትን ፡ እርግጠኛ ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ በበጀት ፡ አዋጁ ፡ ውስጥ ፡ የተፈቀደውን ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ተጨማሪ ፡ በጀትንና ፡ ዝውውሮችን ፡ ይይዛል ። መግለጫው ፡ በተጨማሪ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የበጀት አርእስት፡ንዑስ፡አርእስትና፡ንዑስ፡አርእስት ፡ ዝርዝር ፡ የተያዘውንና ፡ የወጣውን ፡ እያወዳደረ ፡ ልዩነቱን ፡ ያሳያል ። የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩም ፡ ከመግለጫው ፡ ጋር ፡ የሚያያዝ ፡ አንድ ፡ ራፖር ፡ ያዘጋጃል ።

> በመጨረሻ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፰ ፡ መሠረት ፡ "እያንዳንዱ ፡ የበጀት ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ በአራት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የዚያውኑ ፡ የተፈጸመውን ፡ ዓመት ፡ የገቢና የወጪ ፡ ሙሉ ፡ ራፖር ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱና፡ለፓርላሜንቱ፡ያቀርባል። ራፖሩም ፡ ወዲያውኑ ፡ ለዋናው ፡ ኦዲተር ፡ ይላካል ። ኦዲተሩም ፡ በራፖሩ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ለፓርላሜንቱ ፡ ያቀርባል ።"